**የደብረጽዮን መድኃኔዓለም ቤተክርስቲያን ቤተሰብ፤ ሰላም ለእናንተ ይሁን እንኳን ለዚህ አደረሰን!!!**

የኢሊኖይ ስቴት የጤና ጥበቃና መንግስት በሰጠው መመሪያ መሰረት የደብረጽዮን መድሐኒዓለም ቤተክርስቲያን ከ እሁድ ሰኔ 14 (06/21/2020) ጀምሮ ላሁኑ በቁጥር ለተወሰኑ የቤተክርስቲያን አባላት አገልግሎት ለመስጠት እየተዘጋጀ ስለሆነ ከዚህ በታች በተሰጠው መመሪያ መሰረት አገልግሎት ሊያገኙ የሚችሉበት ሰንበት ተመድቦ እንዲያውቁት ስለሚደረግ በሚመጡበት ጊዜ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ መመሪያዎችን እንዲያከብሩ በመድሐኒዓለም ስም እናሳስቦታለን፣፤

1- ቤተክርስቲያን ሊመጡ በተመደበሎት እለት ወይም ሰሞን፣ ትኩሳት ሳል ደጋግሞ ማስነጠስ የጉሮሮና የሥጋሰውነት ሕመም ያሎት ወይም የነበሮት ከሆነ ከቤት በመቆየት ለሌላ የሰንበት እለት እንዲዛወርሎት ያሳስቡ የመተንፈስ ችግር ተጨምሮ ከሆነ የጤና ባለሙያዎችን ያነጋግሩ

2- ቤተክርስቲያን ውስጥ ሳሉ የሚገባውን እርቀት መጠበቅዎን አይርሱ

3 - የጫማ መያዣና መጣያ ከደጃፉ ይኖራል፤ ጫማዎትን ለመያዝ የተጠቀሙበትን ፕላስቲክ ለመጣያ ከተዘጋጀው ውስጥ ይጣሉ

4 - ለዚህ አገልግሎት የተመደቡ አስተናጋጆች ከበር ጀምረው ስለሚጠብቁዎትና የመመሪያና የመቀመጫ ምልክቶች ስላሉ መስተንግዷቸውን በአክብሮት ይቀበሉላቸው።

5 - ባሁን ጊዜ ለእያንዳንዱ እሁድ የሚፈቀደው የአባላት ብዛት 30 ስለሆነ፣ ለዚህም ከቤተክርስቲያን ለጸሎት፣ ለቅዳሴና ለማንኛውም አገልግሎት ለመምጣት ተራ ለማስያዝ ምዝገባ ስላለ ከዚህ በታች ስማቸው ለተጠቀሱት የቤተክርስቲያናችን አገልጋዮች በመደወል እንዲመዘገቡና፣ በመዝጋቢዎች በተሰጠዎት ቀን ብቻ እንዲመጡ ቤተክርስቲያንዎ በትህትና ታሳስባለች ፣፤

1. ወ/ት እናኑ ወንድራድ --------773-818-3707
2. አቶ ፋሲል ደርበው ----------773-507-2129
3. አቶ ሰለሞን ገ/ክርስቶስ--------- 773-255-7449

6 - በወላጆች ቁጥጥር ብቻ የሚያዙ ልጆች ከወላጆች ጋር መምጣት ሲችሉ፤ ይህ ሳይሆን ቀርቶ ባሁኑ ጊዜ ቤተክርስቲያን በቁጥጥር ለመርዳት ስለማትችል ልጆች ወጥተው ለአደጋም ሆነ ለበሽታ እንዳይጋለጡ ማድረግ የቤተሰብ ሃላፊነት ነው።